**እውን ክርስቶስ ኢትዮጵያዊ ነውን?**

(ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው)

ከዓመታት በፊት "ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊ ነው" የሚለውን ጨምሮ ብዙ እንግዳ የሆኑ ነገሮችን የሚናገሩ ሦስት "አባቶችን" አውቅ ነበር አንደኛው ከሀገር ውጭ ናቸው፡፡ እነኝህ "አባቶች" ተከታዮች እያፈሩ መጡና ዛሬ ላይ እነሱ የሚሉትን የሚያምኑ ቁጥራቸው አነስተኛ የማይባሉ ሰዎችን እያየን ነው፡፡ እነዚህን እንግዳ አስተምህሮዎቻቸውንም በማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛ (social media) በከፍተኛ ደረጃ እየናኙት ይገኛሉ፡፡ እውን ግን የናዝሬቱ ኢየሱስ መሲሑ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊ ነው?

ይሄንን ብለው እየሰበኩ ያሉ "አባቶች" ይሄንን ትምህርታቸውን በቀጥታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም ትውፊታዊ መረጃ በመስጠት አያረጋግጡም፡፡ የሆነ የራሳቸውን ነገር ይቀበጣጠሩና ክርስቶስንና ሌሎች ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አባቶችን ሁሉ ኢትዮጵያዊያን ያደርጓቸዋል፡፡ እነኝህ አባቶች ሲያዩዋቸው የአእምሮ እክል ያለባቸው አይመስሉም፡፡ የሚናገሩትን ሲናገሩ እንደማንኛውም ጤነኛ ሰው ተረጋግተውና በቁምነገር ነው፡፡ ነገር ግን የሚሉት ነገር ሁሉ በቁም ያለ ሰው አይደለም የተኛ ሰው እንኳን በቅዠቱ የማይቃዡው የማይቀባጥረው ነገር ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ እኔ በግሌ የሚሉትን ነገር ብቻ ሳይሆን ጤናቸውንም ጭምር ለመጠራጠር ተገድጃለሁ፡፡

በተለይ አንደኛው እቤታቸው ጠርተውኝ ሄጀ ስንጫወት ስናወጋ ስለ ታቦተ ጽዮን አነሣንና "ታቦተ ጽዮን ማለት አሉና ከአልጋቸው እራስጌ በኩል ያለችውን የኪሊዮፓትራን ጉርድ የተቀለመ የሐውልቷን ፎቶግራፍ (ምስለ አካል) እያሳዩኝ ይህች ናት" ካሉኝ በኋላ ምንም እንኳን በቁም ከሚያቃዡቸው ከሚያስቀበጣጥራቸው ውጭ "ልብስ እንደመጣልና የመሳሰሉትን" የአእምሮ እክል ያለበት ሰው የሚያደርጋቸውን ድርጊቶች የሚያደርጉ ባይሆኑም ጤነኛ አለመሆናቸውንና መነኩሴ ነኝ ቢሉም፤ ሰውም ምንኩስናቸውን ቢያምንም፤ ኢአማኒ መሆናቸውን ጭምር ለራሴ አረጋግጫለሁ፡፡ እጅግ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር እነኝህን "አባቶች" የሚያምናቸውና የሚከተላቸው ሰው መገኘቱ ነው፡፡

ሲመስለኝ እነኝህን ሰዎች እንዲህ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ያላቸው ፍቅር እጅግ መብዛቱ ከልኩ አልፎባቸው ተለክፈው ነው የቁም ቅዠት ውስጥ የገቡት፡፡ ብቻ ግን ይገርመኛል የሀገር ፍቅር ለአንዱ እንዲህ በዝቶበት የቁም ቅዠት ውስጥ ድረስ ሲጥለው ለሌላው ደግሞ እንጥፍጣፊ እንኳን አጥቶ ጉርቦዋን ፈጥርቆ አንቆ ሊገላት ያንፈራግጣታል፡፡ የሚያሳዝነው ሁሉም ግን በአንድ አፈር ላይ ተወልደው ያደጉ ከአንድ ውኃዋ የጠጡ ናቸው፡፡ በግል ጥረቱ ካልሆነ በስተቀር ሀገሪቱ እራሷ አንደኛውን ከሌላኛው ለይታ ያደረገችለት ምንም ነገር የለም፡፡ እንዲያውም የሚገርመው ነገር ብዙ ጊዜ ሀገር ፍቅር ስሜቱ እንደነገሩ ሆኖ የሚታየው በለም ጎኗ ያሳረፈችው ዜጋዋ ነው፡፡ በተጎዳው ጎኗ ያሳረፈችው ደግሞ በፍቅሯ ሲዋትት ይታያል፡፡ እንዲህ ብሎ መደምደም ግን አይቻልም፡፡ በተለይ መዚህ ዘመን በተጎዳው ጎኗ ያረፈው ነው ለጥፋቷ እጅግ ሲኳትን እያየን ያለነውና፡፡

እናም ይሄ ከልክ ያለፈው የሀገር ፍቅራቸው በዓለም መድረክ ላይ ትልልቅ ዋጋ ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ኢትዮጵያዊ እንዲያደርጉ ያስገድዳቸዋል ይጫናቸዋል፡፡ አሁን አሁንማ ጭራሽ ለይቶላቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊ እንደሆነ የማይሰብክ የማይናገር የማይገልጥ የማይመሰክር መጽሐፍ ሁሉ የሰይጣን ነው በማለት መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ ሁሉንም የቤተክርስቲያን መጻሕፍ አራክሰዋል አጣጥለዋል አስተህቅረዋል ክደዋል፡፡ መቸም ሰይጣን ሲፈትን ጠልፎ ለመጣል ሲፈልግ በምንወደው በሚገንብን ነገር ነውና የሚመጣው እነኝህንም አባቶች ለመጣል ሲፈልግ በሚወዱት ነገር መጣባቸው፡፡ ሰይጣን በምንወደው ነገር የሚመጣብን በቀላሉ ለመጣል ስለሚያስችለው ነው፡፡ ለዚህም ነው መጽሐፉ "ሰው በወደደው በዚያ ይጠፋል" ማለቱ፡፡ እነኝህን የካዷቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ከጣሉ በኋላ እንዴት ብለው ምን ይዘው ክርስቲያኖች (ሃይማኖተኛ) ነን ሊሉ እንደሚችሉ አላውቅም፡፡

እነዚህ ሰዎች ከዚህ የለየለት የክህደት አቋም ላይ ከመድረሳቸው በፊት የት እንደነበሩና እንደቀልድ እንደዘበት በጀመሯት እብለት ሰይጣን እንዴት አድርጎ በትንሽ በትንሹ ቀስ በቀስ እየሳበ ወስዶ ዛሬ ካሉበት የክህደት ማጥ ውስጥ እንደከተታቸው መለስ ብለው ቢያዩት ለራሳቸውም ቢሆን ሳይገርማቸው የሚቀር አይመስለኝም፡፡ አሁን ላይ ደግሞ ጭራሽኑ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን አውግዘው በመለየት "ኢትዮጵያይ ዐምሐራይ" የሚባል ሃይማኖት ያሉትን ድርጅት መሥርተው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ምን ይደረግ? እንግዲህ ክርስቶስ በቃሉ በማቴ. 24፤1-28 ላይ የዘመኑ መጨረሻ (የጌታ መምጫ) ሲቃረብ ሐሰተኛች መምህራን ሐሰተኞች ነቢያት ይመጣሉ በየአልፍኙ (አዳራሹ) ሐሰተኞችን ክርስቶሶች ይሰብካሉ ብሏልና ይህ ይፈጸም ዘንድ ግድ ነው፡፡

ከቅዠቱ ወጥተን ወደ እውነታው ስንመጣ ወደዱም ጠሉም ኢየሱስ ክርስቶስ በደም ኢትዮጵያዊ ነው ብሎ እራሱን በማታለል የራሱን ውሸት የሚያምንና የሚሰብክ ሰው በእርግጠኝነት በኢየሱስ ክርስቶስ አያምንም አያውቀውምም፤ እውነትም በውስጡ የለም፡፡ ምን እየሠሩ እንደሆነ የማያውቁ እነኝህ ቃዣታሞች ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊ ነው ብለው ሲደርቁ ምን ማለታቸው እንደሆነ እንኳን አያውቁም፡፡ ኢትዮጵያዊ ካልሆንክ በስተቀር ልናምንህ እንቸገራለን እያሉ ነው፡፡ ይሄ የዘረኝነት በሽታ ነው፡፡

ሲጀመር የሀገርና የዘር ልዩነት አጥር የሚሠራውና የሚያሳስበው ለእኛ ለሥጋዊያኑ እንጅ ለእግዚአብሔርና ለመንፈሳዊያኑ አይደለም፡፡ እግዚአብሔርና ሥራዎቹ በዘርና በሀገር ከተወሰኑ ወይም የአንድ ሀገርና ሕዝብ ብቻ እንደሆኑ ከተቆጠሩ የመላው ዓለም መሆን አይችሉም፡፡ ይሄ ደካማ አስተሳሰብ ነው፡፡ ዘረኝነት የእኩያን ሰዎች ችግር እንጂ የፈጣሪ አለመሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ለምን ነጭ ሆነ ስለሆነም እኛ አፍሪካዊያኑ ጥቁሮች፣ ሩቅ ምሥራቃዊያኑ ቢጫዎችና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ያሉቱ ቀዮች እሱን ልናመልክ አይገባም አይባልም፡፡

እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቃቹህ ክርስቶስ በሁሉም የሰው ዘርሮች ሁሉ የዘረኝነት ጥያቄ ሳይነሣበት ያለልዩነት እንዲመለክ ከነማን መወለድ ነበረበት? ከጥቁሮቹ? ከቢጫዎቹ? ወይስ ከቀዮቹ? ወይስ እንደ ውኃ ቀለም አልባ ሆኖ መምጣት ነበረበት? የግድ ደግሞ ከሰው መወለድ እንደነበረበት አትርሱ፡፡ ከነጭ ሳይሆን ከሌሎቹ ቢወለድ ኖሮ በእኩያን ሰዎች አሁን እየተነሣ ያለው ቅሬታ (የዘረኝነት ጥያቄ) ሳይነሣበት መመለክ ይችል ነበር ወይ?

ስለዚህ ይህ ችግር ሰይጣን ያሳሳታቸው የእኩያን እንጂ የፈጣሪ አይደለም፡፡ ፈጣሪ የሚያውቀው አንድ አዳምን መፍጠሩንና ሁላችንም የሱ ልጆች መሆናችንን ነው፡፡ የቆዳ ቀለም ልዩነቱን የፈጠረው የአየር ንብረት ነውና ጥቁሩም፣ ነጩም፣ ቢጫውም፣ ቀዩም እንዲያ በመሆኑ ሊያፍር ወይም ሊኮራ ሊወቀስ ወይም ሊመሰገን አይችልም አይገባምም፡፡ ራሱን የፈጠረ የለምና፡፡ የእግዚአብሔር ወገንም ጠላትም መሆን የሚቻለው በሥራችን እንጅ በደም አይደለም ከአዳም ያልሆነ የለምና፡፡ ለዚህም ነው ክርስቶስ በወንጌሉ "የአብርሃም ልጆች ከሆናቹህ የአብርሃምን ሥራ ሥሩ፡፡ የአብርሃም ልጆች ነን በማለት የምትድኑ አይምሰላቹህ" ያለው፡፡

እነዚህ በቁማቸው የሚያቃዡቸው ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በደም ኢትዮጵያዊ ነው ሲሉ ከአብርሃም እስከ ዮሴፍ ያሉትን በክርስቶስ የዘር ኃረግ ወይም ትውልድ ያሉ 41 አባቶችን ሁሉ ኢትዮጵያዊያን ናቸው እያሉ እንደሆነ ልብ አላሉትም፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ደግሞ ዕብራዊያን (እስራኤላዊያን) እንደሆኑ በግልጽ ያትታሉ፡፡ ሁሉንም ነገር በጭፍን ኢትዮጵያዊ የማድረግ አባዜ የከፋ የኢአማኒ አስተሳሰብ ነው፡፡ በውስጡ የመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን የሰይጣን የሆነ ስግብግብነት ስስትና ለእኔ ብቻ የሚል ክፉ ስሜት የታጨቀበት ነውና፡፡ ይሄንን እንዲሉ የሚያስገድድ ምንም ነገር የለም፡፡ ከማንም የቀደመ አምላኮ እግዚአብሔር አለንና፡፡

ለዚህም ነው የእስራኤል ልጆች እንዳይረክሱ ከአሕዛብ ማለትም ከፍልስጥኤማዊያን፣ ከኢሎፍላዊያን፣ ከእስማኤላዊያን፣ ከኬልቄዶናዊያን፣ ከከለዳዊያን፣ ከሳምራዊያን፣ ከሰርቂሳዊያን፤ ከኬጢያዊያን፣

ከሮማዊያን፣ ከሰጢቃዊያን፣ ከሰርቂሳዊያን፣ ከተንባላታዊያን፣ ከዮናናዊያን፣ ከግብጻዊያን፣ ከአማሌቃዊያን፣ ከሰርቡሳዊያን ባጠቃላይ ከራሳቸው ዘር ውጪ እንዲያገቡ እግዚአብሔር በከለከላቸው ወቅት ሊቀ ነቢያት ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን ሊያገባ የቻለው፡፡ የእኛን ሕዝበ እግዚአብሔርነት አያውቁ የነበሩት ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያምም ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን በማግባቱ «እግዚአብሔር በእኛ ብቻ ተናግሯልን በእሱም የተናገረ አይደለምን?» ብለው አጉረመረሙ፡፡ ነገር ግን እኛ ኢትዮጵያዊያን እንደሌላው ሕዝብ ከአሕዛብ ወገን ሳንሆን ከሕዝብ ወገን ነበርንና ነንምና የሙሴና የሲፓራ ጋብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ አልተጠላም አልተነቀፈም ተባረከ እንጂ፡፡ ሳይገባቸው አጉረምርመው የነበሩት እኅቱ ማርያምና ወንድሙ አሮንም በማጉረምረማቸው በእግዚአብሔር ተቀጡ ዘኁ. 12 ፤1-15 / ዘጸ. 2፣ 16-22 ፡፡

በእርግጥ ወደ ኋላ ላይ ግን ይህ ጉዳይ ማለትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕዝበ እግዚአብሔር መሆኑ በደንብ ግልጽ ሆኖ ተጽፏል፡፡ ለምሳሌ በትንቢተ አሞድ 9-7 ላይ እግዚአብሔር የተናገረውን ብናይ ጭራሽ እንዲያውም እኛ የኢትዮጵያ ልጆች በኩር ነን ከሚሉት ከእስራኤል ልጆች ይልቅ በእግዚአብሔር የተወደድንና የከበርን ሆነን እናገኘዋለን፡፡ ቃሉ እንደሚለው “የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር” በማለት እግዚአብሔር በኩራት ናቸው የሚባሉትን የእስራኤል ልጆችን ልክ እንደ እኛ አድርጎ እንደሚያያቸው ከእኛ አሳንሶ እንደማያያቸው እነሱን በማጽናናት መናገሩ ተጽፏል፡፡ እንግዲህ የእኛ ማንነት በእግዚአብሔር ፊት የተገለጸውን ያህል ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢትዮጵያ ከመቼ ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔርን ማምለክ እንጀመረች የተገለጸ ነገር የለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ስንመረምር ልንረዳ የምንችለው ነገር ቢኖር ከቀደሙት የቀደምን መሆናችንን ብቻ ነው፡፡ ከዚህ የከበረ ምንም ነገር የለም፡፡

አንዳንድ ቅናተኞችና ምቀኞች በመጽሐፍ ቅዱስ “በተደጋጋሚ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እያለ የሚጠራት ይህች አይደለችም ሌላ ናት” የሚለው ክርክር ሙሴ በዘፍ. 2፤13 ላይ ከዐባይ (ግዮን) ወንዝ ጋር በማያያዝ ዐባይ ከእሷ መንጭቶ ፈልቆ ምድሯንም የሚከባት በማለት አሁን ትናንትና ቅኝ ገዥዎች ቱርክና እንግሊዝ መጥተው ድንበራችንን በጣም ወደ ውስጥ እስከገፉብን ጊዜ ድረስ የነበረችውን፤ ኢትዮጵያ እያለ የሚጠራት ብርቅየ ሀገር ዐባይ የደጋን ቅርጽ ሠርቶ ምድሯን እንደከበባት በማሳየት ያለችበት ቦታ የት እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ አሳይቷልና የቅናተኞች የማስተባበያ ወሬ አልሠራም፡፡

እንደ የእግዚአብሔር ሕዝብነታችን ይህ እንዳትረክሱ ከማያምኑ ከአሕዛብ ጋር አትጋቡ የሚለው ክልከላ በእኛም ላይ ይሠራ ነበር አሁንም ይሠራል፡፡ የእኛ ከአይሁዶቹ የሚለየው ክርስቶስ ተወልዶ እነሱ ሳይቀበሉት ሰቅለው ከገደሉት በኋላ እራሳቸው አይሁዶቹ በእኛ ዘንድ ብንጋባቸው ከሚያረክሱን እንዳንጋባቸው ከተከለከልናቸው ወገኖች ቁጥር መጨመራቸው ነው፡፡ ልክ አይሁድ በመጻሕፍት የማይጋቧቸውን ዘሮች ዝርዝር እንደዘረዘሩ ሁሉ አንዳንድ የእኛ የቤተክርስቲያን መጻሕፍትም እንዲሁ በሀገራችን ያሉ ዛሬ ሳይሆን ቀድሞ ከሃይማኖት የራቁ በባዕድ አምልኮ የተተበተቡ ብሔረሰቦችን ወይም ጎሳዎችን ስም እየዘረዘሩ ከነሱ ጋር መጋባት ክልክል መሆኑን ያትታሉ፡፡ ነገር ግን ከነዚያ ብሔረሰቦች ወይም ጎሳዎች ያመነ የተጠመቀ ቢኖርና ጋብቻ ቢፈጸም ችግር እንደሌለበት ይገልጻሉ፡፡ ይሄንን በተሳሳተ አረዳድ በመተርጎም ለተሳሳተ የፖለቲካ (የእምነተ-አስተዳደር) ፍጆታ ለመጠቀም የሚሞክሩ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን ለማንቋሸሽ የሚሞክሩ የማያስተውሉ ወገኖች እንዳሉም ይታወቃል፡፡

ከቤተክርስቲያን ውጭ የሆኑ የተለያየ እምነት ያላቸው ወገኖችም እነዚያን መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ናቸውና አንቀበልም ሲሉ ይናገራሉ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ግን ይሔንን አይልም፡፡ ቃሉ የሚለው “የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው መንገድ ደግሞ ይጠቅማል” ጢሞ. 3፤16-17 ነው የሚለው ቃሉ፡፡

በመሆኑም የቤተክርስቲያን መጻሕፍት 81 ናቸው የለም 66 ናቸው ማለት አይቻልም አይገባም ማለት ነው፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ በወንጌሉ 21፤25 ላይ እንደገለጸው "ኢየሱስ ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል" ይላልና ቅዱሳት መጻሕፍት እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ በሌሎች ሐዋርያት፣ ቅዱሳንና ሊቃውንትም የተጻፉትን መጻሕፍትም እግዚአብሔር በመረጣቸው ቅዱሳንና ሊቃውንት እንደመጻፋቸው ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ አለባቸውና የተቻለንን ያህል የመሰብሰብ ግዴታ አለብን፡፡

ነገር ግን "መጽሐፍ ቅዱስ" ተብለው በአንድ የመጠረዝ ዕድል ካገኙትና መጽሐፍ ቅዱስ ተብሎ ከሚታወቀው መጽሐፍ ላይ፤ ልክ አሁን አሁን "በቀላል አማርኛ፣ አዲስ ትርጉም" እየተባሉ ቀድሞ ከነበረው ላይ የነበረ ለማስመሰል ሌላ ቃል መጨመር ወይም ቀድሞ ያልነበረ ለማስመሰል ቃል መቀነስ ወይም መቆነጻጸል በዮሐ. ራእይ 22፤18-19 ላይ እንደተጻፈው ፈጽሞ የተከለከለና የገሐነም ፍርድ የሚያስጥ ኃጢአት ነው፡፡ ከሌሎችም የቤተክርስቲያን መጻሕፍት ላይ ቢሆን ያው ነው፡፡ መተንተን መተርጎም ማብራራት ግን ይቻላል፡፡ ይህ ቃል ምንም እንኳን እዚያው ጥቅሱ ላይ በግልጽ እንደተገለጸው ግዝቱ የሚያገለግለው ለዚያ "የትንቢት መጽሐፍ" ለዮሐንስ ራእይ ቢሆንም ግዝቱ ወይም ማስጠንቀቂያው ለሌሎች የቤተክርስቲያን መጻሕፍትም ያገለግላል፡፡

እናም የሌለ ነገር መዘባረቅ ፈጽሞ አይገባም፡፡ እግዚአብሔር የእውነትና የፍቅር አምላክ ነው፡፡ ይህ የእውነትና የፍቅር አምላክ በዚህ ድርጊታቸው ቢያዝን ቢከፋ እንጅ አይደሰትም፡፡ በእጅጉም ይታዘበናል፡፡ እንደዚህ ባለ የሐሰት፣ የስግብግብነት፣ የስስትና የስርቆት መንፈስ በነገሰበት ልብ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጽሞ አያድርም የከፉው መንፈስ እንጅ፡፡

ካቶሊኮች እግዚአብሔርን ያከበሩ ያስደሰቱ መስሏቸው እናቱን እመቤታችንን "ኃይለ አርያማዊት" (የሰው ልጅ ያልሆነች) ናት በማለት የሠሩትን ስሕተትና ክህደት እነኝህም ከጉያችን ያሉ የነበሩ "አባቶች" በሌላ መልኩ ደግመውታል፡፡ እግዚአብሔር በሐሰት ሥራ አይከብርም አይደሰትምም፡፡ እንዲህ ብለን ካሰብን ገና አለማመናችንን እንወቅ፡፡ ቅዠት ቅዠት እንጅ እምነት ሊሆን አይችልም፡፡ በሌላ በኩል ይሄ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ንቀትም ነው የሚያሳየው፡፡ ይህ እንቅስቃሴ በቸልታ ሊታይ የሚገባው አይደለም፡፡ እምነት እንዲህ ቀልድ አይደለም በእውነት እንጅ በስሜትም አይነዳም፡፡ እኔ ይሄንን ሁሉ ድርጊት በእግዚአብሔር እንደመቀለድ እንደማሾፍ አው የምቆጥረው፡፡

በሌላ በኩል ይህ እንቅስቃሴ የማይሆንና የማይመስሉ ነገሮችን እየተናገሩ በመጽሐፍ ቅዱስና በዓለም ታሪክ እንደነ ሔሮዱትስና ሆሜር ያሉ ከማንም ሀገር በላይ አልቀው በመጻሕፍቶቻቸው የመሰከሩላትን ታላቅ ሀገር ኢትዮጵያንና ታላላቅ ሥራ እንደሠሩ የተነገረላቸውን በትክክልም ኢትዮጵያዊያን እንደሆኑ የሚታወቁትን የዋኖቻችንን ታሪክ ሁሉ ተረት ለማስመሰል የሚሠራ ሴራም ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ አባቶች ዋነኛው የነበረውን አባት እንይ፡፡ ሕዝበ እስራኤልን ከእግዚአብሔር ጋር ያስተዋወቃቸው አብርሃም እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አብርሃምን የባረከውና አብርሃምም ዐሥራትን ለእሱ ያወጣለትና አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋራ ከመተዋወቁ እግዚአብሐየርን አምላኪ ከመሆኑ በፊት የእግዚአብሔር ካህን የነበረው ግን መልከጸዴቅ ነው፡፡

ይህ ሰው ኢትዮጵያዊ ነበረ ወይም ነው፡፡ በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ትውልዱ አልተገለጸም፡፡ ታዲያ በምን ታወቀ ቢሉ በስሙ፡፡ የመልከጼዴቅ ስም በየትኛውም የዓለማችን ቋንቋ በተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ብታዩ ተቸግረውም ቢሆን የሚያስቀምጡት ያው ራሱ "መልከጼዴቅ" የሚለውን ቃል ነው፡፡ ይህ ስም የግእዝ ስም ነው፡፡ ለሌሎች ቋንቋዎች በተለይም ሴማዊ ላልሆኑት ይህ ቃል ወይም ስም ባዕድ ነው፡፡ ሴማዊያኑ ግን ቃሉን ከግእዝ ወርሰው ይዘዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መልከጼዴቅ ሲናገር "የስሙ ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው፡፡ በኋላ ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው" ብሎ በቋንቋቸው ተርጉሞ ለወገኖቹ ለዕብራዊያን በመልእክቱ አስረድቷል፡፡

በተጨማሪም “እናትና አባት የትምልድም ቁጥር የሉትም” ብሎታል፡፡ ይህን ማለቱ ሰው አይደለም ለማለት ሳይሆን በአይሁድ መጽሐፍ ወይም የትውልድ ኃረግ ዝርዝር ስሙ የለም አልተጠቀሰም ማለቱ እንጅ፡፡ ያልተጠቀሰበትም ምክንያት አይሁድ ባለመሆኑ ነው ይህንንም እዚያው ላይ ገልጾታል፡፡ እንጅ ሥልጣነ ካህነቱና ክብሩማ የሱን የሚያህል ማን ነበር? እንዲያውም “የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ” ብሎም ይጠራዋል “ለዘመኑ ጥንት ለሕይዎቱም ፍጻሜ የለውም” ሲል ይሙትም አይሙትም አይታወቅም ማለቱ ነው፡፡ ዕብ. 7፣1-3

ሌላኛው መልከጼዴቅ ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚጠቁመው መላምት ከዘመነ ሐዲስ በፊት እግዚአብሔርን ያመልኩ እሱም ሕዝቤ ይላቸው የነበሩት ሕዝቦች የእስራኤልና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብቻ ነበሩ፡፡ እናም መልከጼዴቅ እስራኤላዊ ካልሆነ ሊሆን የሚችለው ኢትዮጵያዊ ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም እግዚአብሔርን በማምለክ ከእስራኤላዊያንም እንቀድማለን ማለት ነው፡፡

እናም እኛ ኢትዮጵያዊያን ወይም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በቀጥታና በተዘዋዋሪም እስራኤላዊያንን ሕዝበ እግዚአብሔር እንዲሆኑ በማድረግ አኳያ ከፍተኛ ሚና መጫወታችንን መረዳት ይቻላል፡፡ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ብቻም ሳይሆን የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓትንና ሕግንም ጭምር ለእስራኤላዊያን አስተምረናል፡፡ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በእግዚአብሔር ተመርጦ ሕዝቡን ከግብጽ አውጥቶ እየመራ ወደ ምድረ ርሥት በሚወስድበት ወቅት ሕዝቡን ማስተዳደር መዳኘት ለሕዝቡና ለራሱም አስቸጋሪና አድካሚ ሆኖ ነበር፡፡

አማቱ ኢትዮጵያዊው ካህን ዮቶር ወይም ራጉኤል ይህ ሙሴ እያደረገ ያለው ነገር ትክክል ያልሆነና ለሕዝቡም ለራሱም አድካሚ ሥራ አስፈቺ መሆኑን አስረድቶ ከሕዝቡ የነቁ የጠነቀቁትን ሰዎች እንዲመርጥ ከእነሱም የሺ የመቶ የሃምሳ የዐሥር አለቆችን እንዲሾምላቸውና በሕዝቡ ላይ እንዲፈርዱ እንዲዳኙ፤ አውራውንና የሚከብዳቸውን ጉዳይ ብቻ ወደ አንተ ያምጡ ብሎ መክሮ በዚያ መሠረት በአንድ በሙሴ ብቻ ሙሉ ቀን ሥራ ፈተው ሲዋትቱ የነበሩበትን አሠራር ቀይሮ የተሳለጠና የተደራጀ ምቹ የአስተዳደር ሥርዓት እንደሠራላቸው ይህም አሠራር ዛሬ በመላው ዓለም ላለው ሁሉ ተዳርሶ እነሆ እየተጠቀመበት እንዳለና መሠረት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ዘጸ. 18፣13-27.

በዓለም ሥልጣኔና ሃይማኖት ላይ የእኛ ድርሻ ዋነኛውን ስፍራ ይይዛል፡፡ ከዚህ አኳያ ያለን ክብር ከበቂ በላይ ነው ይሄንንም አላምንላቹህም ብሎ ዓለም በሽፍጥ ፊቱን አዙሮብናል፡፡ ያለን ይበቃናል ለሌሎችም እናስብ፤ እግዚአብሔር እኛን ብቻ አልፈጠረም፡፡ ሁሉም የሰው ዘሮች የእግዚአብሔር የእጁ ሥራዎች ናቸው፡፡ ክርስቶስ የሞተው ለእኛ ብቻ አይደለም ለመላው ዓለም ሕዝብም እንጅ፡፡ ኢየሱስ ኢትዮጵያዊ እንዳልሆነ እያወቅን በግድ ኢትዮጵያዊ ለማድረግ መሞከር ሀገርን የመውደድ መገለጫ ሊሆን አይችልም፡፡ ሐሰት ለምንም ነገር ቢሆን የጸና መሠረት ሊሆን አይችልምና፡፡ እንዲህ ብሎ በከንቱ ከመድረቅ ይልቅ ኢየሱስ ክርስቶስ በዳዊት ልጅ በጠቢቡ ሰሎሞን እናት በቤርሳቤህ በኩል ኢትዮጵያዊ ደም አለበት ቢባል መልካምና ተአማኒም ነበር፡፡ የሰሎሞን እናት የኦርዮ ሚስት የነበረችው ቤርሳቤህ ኢትዮጵያዊት ናትና፡፡ ሰሎሞንም ራሱ በመኃልይው “እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ እኔ ጥቁር ነኝ፤ ነገር ግን ውብ ነኝ፤ እንደ ቄዳር ድንኳኖች እንደ ሰሎሞን መጋረጃዎች ፀሐይ መልኬን አክስሎታልና ጥቁር ስለሆንኩ አትዩኝ” ብሎ ተናግሯልና መኃልየ መኃልይ ዘሰ. 1፤5-6.

ወይ ደግሞ እንደ መጣቅ (ሳይንስ) አባባል ዘመናዊው የሰው ልጅ ዘር የዛሬ 100 ሽህ ዓመታት አካባቢ አዲስ አበባ አካባቢ ወጥቶ መላውን ዓለም አዳርሶታል ይላልና ክርስቶስ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሰው ኢትዮጵያዊ ነው ማለትም አንድ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን መጣቅና ሃይማኖት የተለያዩ ብዙ ጊዜም የማይግባቡ ናቸውና የመጣቅን መረጃ ለሃይማኖት መጠቀም የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ስላሉ አስቸጋሪ ነው፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!